# የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታውን አስመልክቶ በጉባኤው የበላይ ጠባቂ አባቶች የተሰጠ መግለጫ

**ለተከበራችሁ የሀገራችን ህዝቦች**

ከሁሉ በማስቀደም በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች በንፁሀን ወገኖቻችን ላይ በተፈፀመው የግፍ ግድያ የተሰማን መሪር ሀዘናችንን እየገለፅን ለሟች ወገኖችና ቤተሰቦች መጽናናትን እንመኛለን።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በፌዴራል መንግስትና በትግራይ ክልል መንግስት መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ውጥረትና መካረር ገደቡን አልፎ ግልጽ  የሆነ ወታደራዊ ግጭት መጀመሩ በእጅጉ አሳዝኖናል። ይህ እንዳይሆን በማሰብ ሁለቱን አካላት አቀራርበን ለማወያየት ያደረግነው ጥረት ለጊዜው ሳይሳካ በመቅረቱም በእጅጉ አዝነናል።

ልዑል ፈጣሪያችን የሰውን ልጅ ሲፈጥረው ታላቅ የማስተንተንና የማስተዋል ጥበብንና ፀጋን የቸረው ሲሆን ይህም ያለፈውን ከመጭው በማዛመድ አሁናዊ ሁኔታውንና አኗኗሩን ለማስተካከል  ያስችለዋል።

ጦርነት በባህሪው አውዳሚና አጥፊ ነው። ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊና የኢኮኖሚ ኪሳራን የሚያስከትል የመጥፎዎች ሁሉ መጥፎ አማራጭ መሆኑን ልናስታውሳችሁ እንወዳለን። በተለይም በአንድ አገር ወንድማማቾች መካከል የሚፈጠር ግጭት ማንንም አሸናፊ የማያደርግ አስከፊ ተግባር ነው።

ስለሆነም ሁሉም ወገን ለሀገርና ለወገን ደህንነትና ሰላም ቅድሚያ እንዲሰጡ እያሳሰብን የሚከተለውን አባታዊ ምክርና መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።

1. የተከበራችሁ የፌዴራልና የትግራይ ክልል መንግስታት ከሁሉም በፊት ቅድሚያ ለሀገራችን ሰላምና መረጋጋት በመስጠት በመካከላችሁ የተጀመረውን የርስበርስ ወታደራዊ ግጭት ያለምንም ቅደመ ሁኔታ እንድታቆሙ በአጽንኦት እንጠይቃለን።
2. የተከበራችሁ የብልጽግና ፓርቲ እና የህዋሓት ፓርቲ አመራሮች በመካከላችሁ የተፈጠረው የፖለቲካ ልዩነት በመነጋገር የሚፈታ ስለሆነ አሁንም በጉዳዮቻችሁ ላይ በግልጽ በመነጋገር እንድትፈቱት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

3. የተከበራችሁ በየደረጃው የምትገኙ የሃይማኖት አባቶች በሁለቱ አካላት የተጀመረው የርስ በርስ ወታደራዊ ግጭት አስከፊ ውጤት እንደሚያመጣ ተገንዝባችሁ ችግሩ በሰላማዊ ውይይትና ድርድር እንዲፈታ አባታዊ ኃላፊነታችሁን እንድትወጡ አደራ እንላለን፡፡
4. የተወደዳችሁ የሀገር ሽማግሌዎችና፣ አባገዳዎች፣ አባቶች/እናቶች እና ተጽእኖ ፈጣሪ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ በወንድማማቾች መካከል የተጀመረው ግጭት እንዳይባባስና ሁለቱም ወገኖች ወደ ሰላማዊ ድርድር እንዲመጡ በጎ ተጽዕኖ እንድትፈጥሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡
5. የተከበራችሁ የመገናኛ ብዙሀን ድርጅቶች ይህ ግጭት በሁለት ወንድማማቾች መካከል የሚደረግ መሆኑን ተረድታችሁ ጉዳዩን በጥንቃቄና በከፍተኛ በኃላፊነት ስሜት እንድትዘግቡ አባታዊ የአደራ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን፡፡
6. የተወደዳችሁ ወጣቶች በኢትዮጵያዊያን ወገኖች መካካል የተፈጠረው ግጭት በወንድማማች መካከል የተፈጠረ መሆኑን ተገንዝባችሁ ችግሩን ከሚያባብሱ ሁኔታዎች እንድትቆጠቡ አደራ እንላለን፡፡
7. የተከበራችሁ የጸጥታ ኃይሎችና አመራሮች የተፈጠረውን ሁኔታ በከፍተኛ ጥበብና ማስተዋል እንዲሁም በሆደ ሠፊነት እንድትይዙት የአደራ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን፡፡
8. የተከበራችሁ የማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎች በማህበራዊ ትስስር ገጾች የምታስተላልፉት መልዕክት ችግሩን ከማባባስ የተቆጠበና በአንጻሩ ለሰላም ጥሪ የሚያደርግ እንዲሆን እናሳስባለን፡፡

በመጨረሻም በሀገራችን የሚታየው የጥላቻና የክፋት መንፈስ እንዲወገድ ሁላችንም እንደየእምነታችን ሥርዓት ፊታችንን ወደ ፈጣሪ በመመለስ ከነገ ጥቅምት 26 ጀምሮ ለ1 ሣምንት የሚቆይ የጸሎት እና የምህላ ጊዜ መሆኑን አውቃችሁ በፀሎት እንድትተጉ አደራ እንላለን፡፡

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ!

ለሀገራችን ሰላም ይሁን!

ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም